# ግልጽ ደብዳቤ ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ

ከገ/ኢ. ጕርፋ

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር፦

የቢ.ቢ.ሲ.ው ማይክ ቶምሶን (Feb. 3, 2005) 'አቶ መለስ፣ ግብፅ ለረጅም ዘመን የአባይ ተፋሰስ ተጠቃሚ ሃገራት በወንዙ ትላልቅ የመስኖ ፕሮጀክቶችን ለማልማት ፈቃድ ሲጠይቁ በምታሳየው የማያቋርጥ ተቃውሞ በየቀኑ እየተናደዱ መምጣታቸውንና... "ግብፅ በአባይ ወሃ ሰሃራ በረኻን ወደ ፍፁም አረንጓዴነት ለመለወጥ ስትችል፣ እኛ የወሃው 85% አፍላቂ ሃገር፣ ኢትዮጵያውያን፣ ወሃውን ለራሳችን እንዳንጠቀምበት ተከልክለናል። ስለዚህም በየዓመቱ የዳቦ ለማኞች እንድንሆን ተገድደናል..."አሉ'[1] ሲል ዘግቧል።

ይህ ኢፍትሓዊነት ለማመን እጅግ አዳጋች ነው። ከአንድ ዓመት ገደማ በፊት ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ አንድ ጽሑፍ[2] አቅርቤ ነበር። ከዚህ በበለጠ ዘርዘር አድርገው የጻፉትና በማስረጃነትም የሚጠቀስ፣ ዶ/ር ገብረ ጻድቅ ደገፋ፦ *አባይ፦ ታሪካዊ፣ ሕጋዊና ልማታዊ አቅጣጫ፣ ለ21ኛው ምዕተ ዓመት ማስጠንቀቂያ እንዲሆን የተጻፈ* (***The Nile: Historical, Legal and Development Perspective, Written as a Warning for the Twenty First Century***)[3] በሚል ርዕስ ያቀረቡትን እንዲመለከቱ እለምንዎታለሁ።

ግብፅ ወሃችንን ጠጥታ በመርካቷ፣ ለደጉ ውለታችን መልስ በእጅ-አዙር ጦር ኢትዮጵያን ስትወጋንና የደም ክፍያ ስታስደማን ቆይታለች። በአባይ ወሃ ላይ ያላትን የበላይነት ለማረጋገጥና የኛም ባለመብትነት ተዳፍኖ እንዲቀር፣ የኢትዮጵያን አያሌ ጠላቶች በኅቡዕ ስትደግፍ የኖረች ሃገር ናት። ግብፅ፣ ለብዙ ዓሰርት ዓመታት ለኤርትራ የተገንጣይ ኃይላት ደጀን ነበረች። ግብፅ፣ ሶማልያ፣ እኤአ በ1978 ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜም ደጀን ሆና ከጐኗ እንደቆመች አይዘነጋም። ግብፅ፣ ከኦነግ ጀርባ ደጀን ሆና ቆማለች። ግብፅ፣ የኢትዮጵያንና የሌሎች የናይል ፈሰስ ሃገራትን ኅልውና ለማናጋት ያላትን ጥረት ፈፅሞ የማታቋርጥ ሃገር ናት። ለምሳሌም በዩጋንዳ 'ዘ አርሚ ኦፍ ጎድ' (The Army of God) የተባለውን ኅቡዕ ግንባር የምትረዳ ደጀን አገር ናት።

ጥንት ተነድፎ አሁንም በሥራ ላይ የሚውል ያለው የግብፅ ፖሊሲ[4]፤ አባይን ለማልማት የተረጋጋ አቋምና ሰላም እንዳይኖራቸው፣ መላው የናይል ተፋሰስ ሃገራትን በማያቋርጥ የእርስ በርስ ጦርነትና ቀውስ እንዲዘፈቁ ማድረግ ሞያዋ ነው። ግብፅ ይህን ጨዋታዋን እስካሳካች ድረስ ኢትዮጵያንም ሆነ በተፋሰሱ አካባቢ ያሉትን ማንኛቸውም ሃገራት መውረር አይኖርባትም። እነዚህስ ሃገሮች ሃገር አለን ማለታቸው ምንዋጋ አለው? ኢትዮጵያ ላለፈው ዓሰርት ዓመት ያህል በሰላማዊና በተረጋጋ መንገድ እየሄደች የመምጣቷ ሁኔታ ግብፅን እጅግ እያሰጋት በመሄዱ፣ ይኸው ዛሬ ደግሞ በወታደራዊ

ኃይል የማስፈራራት ዘዴዋን ጀምራለች። ግብፅ የኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት ፈጽሞ ልታያቸው ከማትፈልግ ነገሮች ዋነኛው ነው።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆይ፣

አንድ ጥያቄ ብቻ አለኝ፤- ከመቼ ወዲህ ነው ኢትዮጵያ ከግብፅ የበላይ ተጠባባቂነት ስር (Protectorate) የገባችው? ይህ ካልሆነማ ኢትዮጵያ የራሷ የሆነውን ወሃ ለማልማትም ይሁን ለመጠቀም የግብፅን መልካም ፈቃድ መጠይቋ፣ ይባስ ብሎም መከልከሏ ታድያ ምን ይባላል? እርግጠኛ ነኝ የአያት፣ የቅድመ-አያቶቻችንን ታሪክ በሚገባ ያውቁታል፡ ኃይለሥላሴ፣ ምኒልክ፣ ዮውሐንስ፣ አሉላ፣ ቴዎድሮስ... ሌሎቹም። ከነርሱ ማናቸውም ቢሆን እስከዚህ ድረስ ወደታች አዘቅዝቀና አጎብድዶ በኢትዮጵያ መሬት ውስጥ የተንጣለለውን ወሃ ለማልማትም ይሁን ለመጠቀም የግብፅን መልካም ፈቃድ የሚጠይቅ፣ ጠይቆም የሚከለከል አንዳቸውም አይኖርም።

ለምንድነው ኢትዮጵያ ባልተካፈለችበት ወይም ባልፈረመችበት ጉዳይ፣ በግብፅና በእንግሊዝ መካከል፣ ወይም በማናቸውም ሌሎች ሁለት ሃገራት መካከል ለተደረገ ስምምነት ዕውቅና የምትሰጠው? ሌሎች የናይል ተፋሰስ ሃገራት እንዲህ ያሉትን ስምምነቶችን አልተቀበሏቸውም። ኢትዮጵያም ብትሆን ዕውቅና መስጠት አይገባትም። ማንኛዎቹም የዚህ ዓይነት ሰነዶች ካሉ መቀዳደድና በተገቢ ቦታቸው ማስቀመጥ ይገባል፡ -- በቆሻሻ መጣያ። እንግድያውማ የምን የ<u>ፈቃድ ጥያቄ</u> ነው?

ምኒልክ፣ በአንቀፅ 17 የውጫሌ ውል፣ ኢትዮጵያ ከሌሎች የውጭ ዓለማት ለምታደርጋቸው ማንኛችውም የዲፕሎማቲክ ግንኙነት በኢጣልያን መልካም ፈቃድና አስፈጻሚነት ነው መሆን ያለበት ስለምትል አንዲት ነጠላ ሐረግ አይደለም እንዴ ጋሻ-ጠሩን አንስቶ የተዋጋው! በእንዲህ ዓይነት መንገድ እኮ ነው የኢትዮጵያን ነጻነትና ሉዓላዊነትን ያረጋገጠው። ኢትዮጵያ ይህን ፈቃድ በመጠየቋ ብቻ፣ ከግብፅ የበላይ ተጠባባቂነት ስር መውደቋ ለማንኛውም ሰው ግልፅ አይደለም እንዴ?

ይህ የድፍረት ድፍረት፣ ፍጹም ኢፍትሓዊ የሆነ፣ በጭራሽም ሊታገሱት የማይገባዎት ጉዳይ ነው። አሁን የወሃ ጥያቄ መሆኑ ቀርቶ የሃገር ሉዓላዊነት ጉዳይ ሆኗል። ለመሆኑ ኢትዮጵያ የግብፅን ፈቃድ መጠየቋ በምን ዓይነት መንገድ፣ እንዴትስ ሊሆን ቻለ?


**መፍትሔስ ይኖረዋል?**

እስቲ ይህን አንድ አዲስ ሓሳብ ላቅርብ። ከኢትዮጵያ ከሚሄደው ከዚያ ሁሉ ወሃ፣ ኃይለኛ የፀሐይ ዋዕይ ባለው በረሃ ውስጥ በሚያደርገው የጉዞ እርዝማኔና በሚፈጠረውም ትነት የተናሳ 4% ወይም ከዚያ ያነሰ ወሃ ብቻ እስከ አስዋን፣ ግብፅ መድረሱ ይታወቃል።(5) እንግዲያውስ በሚገባ ቢያዝ በአባይ ወንዝ ሰው፡ 'ይኸን ያህል የወሃ መጠን ለመሆኑ ምን

ይደረግበታል' ብሎ መገመት እስከሚሳነው ድረስ አያሌ ወሃ እንዳለ ግልፅ ነው። የግብፅን የጦርነት ጥማትና የጠብ አጫሪነት ወደ ጎን ተብሎ በእርጋታ የሚያስብ ጭንቅላት ቢገኝ ይህን የፖለቲካ ችግር፣ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ በሚገባ የሚያረካ አንድ የቴክኒካዊ መፍትሔ ሓሳብ ቀጥሎ ልግለጽ፦

በተባበረው የአሜሪካ ግዛት ብቻ የተዘረጉ ከ 200,000 ማይል የሚበልጡ[6] ፈሳሽ ፔትሮልየም፣ ፈሳሽ ጋዞችና ድፍድፍ ዘይት፣ እነዚህም በከፍተኛ ደረጃ ለአደጋ የተጋለጡና በቀላሉ የሚቀጣጠሉ መሆናቸው ብቻ ትተን፣ በሕይወት ለመኖር ጠቃሚነታቸው ከወሃ ጋር ሲመጣጠን እጅግ በጣም ያነሰ ፈሳሾች የሚጓዙባቸው የነዳጅ ቧምቧዎች ናቸው። ይህ እንደዚህ ሆኖ እያለ ታዲያ ለምንድነው 10% የሚሆነውን ወሃ (ግብፅ ከምታገኘው ካለች ከዕጥፍ በላይ የሚበልጠውን) በቧምቧ አገናኝቶ በቀጥታ ከኢትዮጵያ መውሰድ ችግር የሆነው? ኢትዮጵያ ከቀሪው 10% የሚሆነውን ወሃ ደግሞ ለፈለገችው ጉዳይ ብታውለው፣ የቀረው 80% በዚያው ለብዙ ሺሕ በሚቆጠር ዓመታት ሲጓዝ በነበረበት ወንዝ፣ በዚያ መስመር ለሚገኙ የሕይወት እንቅስቃሴዎች ምንም ጉዳት ሳያስከትል፣ በመልክዓ መሬቱም ምንም ተጽዕኖ ሳይኖረው እየጐረፈ መውረዱን ይቀጥላል።

በዓለም ያሉ አያሌ የነዳጅ ቧምቧዎች በተራራማና በረባዳው የመልክዓ ምድር አቀማመጥ ሲወጡና ሲወርዱ ዘይቱን ሽቅብ የሚግፉ የኤሌክትሪክ ኃይል ያስፈልጋቸዋል። አባይን በተመለከተ ግን፣ ከጣና ሃይቅ እስከ አስዋን ግድብ ሲለካ፣ ከ2000 ማይል የማይበልጥ፣ ከዚያም እስከ ካይሮ እንብርት ድረስ ላለው 500 ማይል ሲጓዝ፣ በመሬት የስበት ኃይል ብቻ እንቆልቁሎ በመፍሰስ ይወርዳል።[7]




ይኸ የቧንቧ ወሃ ፕሮጀክት፣ "...ሃገራዊ ሕብረትና የጋራ ጥቅም ግንኙነት ለመሥራት በናይል ተፋሰስ ሃገራት መካከል ሊኖሩ የሚገቡ የሚያጓጉ ግቦች" በሚል፣

በናይል ተፋሰስ ሃገራት አዲስ ሓሳብ አመንጪ (The Nile Basin Initiative)[8] የመክፈቻ ጽሑፍ በተገለጸው አነጋገርና መንፈስ ነው መሠራት ያለበት። የሚቀጥለው አመክንዮታዊ (ሎጂካል) ጥያቄ ታዲያ፣ ይህ ፕሮጀክት በማን ገንዘብ ይቋቋም፣ ማንስ ፋይናንስ ያድርገው? የሚለው ነው። የተባበሩት መንግሥታት የሚሌኒየም ልማት ዕቅድ (The Millennium Development Plan of the UN)[9] እንደዚህ ያሉትን ለይቶ፣ በተለይም ጠቃሚነታቸው ጉልህ ለሆኑ ፕሮጀክቶች በብዙ ቢልዮን የሚቆጠር ዶላር ለብቻው አስቀምጧል። ይህ የቧምቧ መዘርጋት ጉዳይም ብዙ ሳይቆይ እውን ሊሆን ይችላል።

እዚህ ላይ ነው ኢትዮጵያና ግብፅ አሳማኝ የፕሮጀክት ፅንሰ-ሐሳብ ነድፈው፣ ወደ ዓለም ባንክ በጣምራነት ቀርበው፣ ለቧንቧ ዝርጋታ የሚያስፈልገውን ውዕሎተ ንዋይ ሊያገኙ የሚችሉት። ይህ መፍትሔ ከግብፅና ከጠቅላላው የዓለም ሕብረተሰብ ባፋጣኝ ተቀባይነት አግኝቶ ወዲያውኑ በሥራ ላይ የማይውልበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

ሌላስ አማራጭ አለን ወይ?

ግብፅ እንደዚህ ያለውን ዕቅድ ለመቀበል ፈቃደኛ ባትሆንና የተፋሰሱ ሃገራትን ሰላም ለማናጋት ባላት ዕቡይ አካሄድና ፍላጎት ልጽና ብትል ግን፣ ልንከተለው የሚገባን ሌላ አቅጣጫም አለን። አሁን ያለነው የቀድሞ ወዳጆች ወደ ጠላትነት፣ ጠላቶችም ወደ ወዳጅነት በሚዞሩበት 'አዲስ ስርዓተ ዓለም' (The New World Order) ተብሎ የሚጠራ ባለው ዘመን ውስጥ ነን። እስራኤል ለወሃው ካላት ፍላጎት የተነሳ ከግብፅ ጐን ልትሰለፍ፤ አሜሪካም እንደዚሁ ኢፍትሓዊ ከሆነችው፣ ከነገር ፈላጊ ጐን ትቆም ይሆናል።

ኢትዮጵያም እንግዴህ በአዲሱ ስርዓትና በካርታው ጨዋታ ጥበብ ጠንክራ፣ በፖለቲካና በዲፕሎማቲክ ዘዴ፣ ሌሎች የናይል ተፋሰስ ሃገራትንም ከጐኗ አሰልፋ፣ በጋራ ጥቅምና በጋራ ጥረትም አስተሳስራ፣ በተባበሩት የዓለም መንግሥታት ሸንጐ መድረክ እሰጥ-አገባዋን ተሟግታ ማሳመን ይኖርባታል። አንዳንድ ጊዜ የዲፕሎማሲ ጥበብ በለሰለሱ ጣቶቿ ተአምር የምትሠራበት ጊዜ አለ። ስለዚህም ወደማያስፈልግ ጦርነት ላለመግባት ይህ የዲፕሎማሲው ጥበብ በጥንቃቄ ሊሞከር ይገባዋል። ግንስ ዲፕሎማሲ ሊያሳካው ላልቻለ ሁሉ መጨረሻው በጦር ሜዳ ፍልምያ ፍጻሜ ማግኘቱ ግዴታ ነው። ኢትዮጵያም ለዚህ ለመጨረሻው ፍልሚያ መዘጋጀት አለባት።

የዲፕሎማሲው ጥረት አልሳካ ባለ ጊዜ ተንኮለኛውን ጠላት በውል የመለየት፣ ለይቶም በስሙ የመጥራትና የመጠቆም፣ ከመገዳደርና ከመጋፈጡም ታልፎ፣ የመጣው ይምጣ ተብሎ ጦር የሚማዘዙበት ጊዜ ደረሰ ማለት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብም ለነዚህ ሁሉ ዘመናት ብዙጎን ጠላቶቹንና ከነሱም በስተጀርባ ያለውን ቀንደኛ ጠላት፣ ከኒህ በርካታ ተቃዋሚ ኃይላት በኋላስ ማን ቆሟል ብሎ ሊያውቅና በውል ሊለይ ይገባዋል። ከጠላቶቻችን ጀርባ የተለያየ ጭንብል ከፊቱ እየለዋወጠ፣ ለጦርነት፣ ለድኽነትና ለረሃብ የዳረገን ያው አንድና ብቸኛው ጠላታችን ማን መሆኑን አናውቅም እንዴ? መሰረታዊ

ድንቁርናና ማይምነት ከኢትዮጵያ ከመወገዱና ሕዝባችን ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ከመማሩ በፊት ይኸኛው ዋና አሳሳቢ ድንቁርና ከስሩ ተመንግሎ የሚወገድበት ጥልቅ ትምህርት ከሁሉም በፊት አስቀድሞ ሊሰጥ ይገባል። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም ስለ ቀንደኛ ጠላቱ ማወቅና መማር አለበት፣ -- ስለ ግብፅ።

ክቡር ሆይ፡

በተጨማሪም የቢቢሲ ዘጋቢው ከዚህ በታች ያለውን እርስዎ መናገርዎን አያይዞ ገልጿል፤ "በየጊዜው የግብፅ ፕሬዘዳንቶች፣ የናይልን ፈሰስ ሃገራት የወሃ ልማት እንቅስቃሴ ቢጀምሩ በወታደራዊ ኃይል እንደሚጠቀሙ አስፈራርተዋል። እኔ ይህን በጉልበታቸው እየተመኩ በወታደራዊ ኃይል ማስፈራራታቸውን ፍጹም ቦታ አይሰጠውም ባልልም፣ አመች አማራጭ ነው ብየ አልገምትም። ግብፅ ኢትዮጵያን የአባይን ወሃ ከማልማት ለማስቀም ከፈለገች ኢትዮጵያን መውረርና ግዛቷ ማድረግ ይኖርባታል፣ ይህን ግን ማንም በምድር ያለ ኃይል ከዚህ በፊት ያልቻለው ነገር ነው።" ዘጋቢውም ለጥቆ፤ ...መለስ ዜናዊ ግን የመነጋገሩ ጊዜ እንዳለፈ ያምናሉ ካለ በኋላ፤ "አሁን ያለው ስርዓት ቋሚ አይደለም። ስርዓቱ እስከ አሁን የቆመው በግብፅ የዲፕሎማሲ ጫና ብቻ ነው። ነገር ግን የአፍሪቃ ሃገሮቸና ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲ ልምምጥ ሰልችተው ተስፋ የሚቆርጡብትና ስርዓቱንም ፍጹም የማይቀበሉበት ጊዜ ይመጣል። ከዚያ በኋላ ወደ ተግባር ይሰማራሉ።"(10) ብለዋል በማለት ይደመድማል።

ይኸው ለብዙ ዓመታት ሕዝባችን በረሃብ፣ በወሃ ጥም፣ ባልተመጣጠነ ምግብም እያለቀ ነው ያለው። በዚህ አዲስ የታሪክ መባቻ ላንድዬና ለመጨረሻ ጊዜ አዲስ ስርዓት የምንይዝበትና አሁን ያለውን ስርዓት የምንቀለብስበት ዋነኛ ጊዜ ደርሷል። ኢትዮጵያ የራሷ ያልሆነ ምንም ነገር አትሻም። ግን የራሷ የሆነውን ደግሞ፣ በተለይ እንዲህ ለመሰለውና ለከበረው ዕቃ አሳልፋ ለማንም አትሰጥም። ያውም የሕዝቦቿን ሕይወትና ደኅንነት በኪሳራና ሞት በመዳረግ! ምን ሲደረግ! ለምንስ ተብሎ? መሞትስ ካለብን -- ለኛ ለኢትዮጵያውያን ሞት እንግዳ ነው እንዴ? ሁሌ በየመንገዱ ጐዳና፣ በየማእዘኑ የማይለየን ወዳጃችንና ጓደኛችን አይደል! -- ዕድሜ በሃገራችን ችግርና ሽብር እየነዙ፣ ወሃችንና መሬታችንን እየበጣጠሱ ለሚወስዱ ሌቦች። እንግዴኽስ ሞት የማይቀርልን ከሆነ በክብር እንሙት። ሕዝቦቻችን በረሃብ፣ ባልተመጣጠነ ምግብና በማያቋርጥ ችጋር ከሚሞቱ፤ ለፍትሕ እየተዋደቁ፣ የራሳቸው የሆነውን ውሃና ንብረትን በይዞታቸው ገብቶ እንዲጸና ለማድረግ እየታገሉ፣ በተከበረ ሞት መሞቱ እጅግ ይመረጣል።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር

እርስዎ ፍጹም ልክ ነዎት። የንግግሩ ሰዓት ካለፈ ቆይቷል። እርምጃ የመውሰጃው ጊዜም እጅግ ዘግይቷል። እርስዎ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የራሳቸው የሆነውን እንደገና ለኛ ይገባል ብለው እንዲነሱና ይህንን ኢፍትሓዊነት ወደ ቀና አቅጣጫ መልሰው መንገድ

**እንዲያስይዙት፣ ሕዝብን ለማዘጋጀት በዚህ በታሪካዊ ቅፅበት ላይ በሃገር መሪነት ደርሰዋል። እርስዎ ያሳዩት ቁጣ፣ (ያ በቢ.ቢ.ሲ. የተዘገበው) በእያንዳንዳችን ኢትዮጵያዊ ሰውነት ተፈጥሮአዊ የትስስር ድርና ሕዋሳት የሚንቀሳቀስ፣ የሚርመሰመስና፣ ዘወትርም የሚነድድ፣ የሚቀጣጠልም የተቀደሰ ቁጣ ነው። ይህ ዓይነቱ ኢፍትሓዊነት እስከ መቸ! ከእንግዲህስ ወዲያ እንዲቀጥል በፍጹም ሊፈቀድለት አይገባም።**

**ይህን ጉዳይ የእርስዎ ታሪካዊ ተልእኮና ግብ ቢያደርጉት ኢትዮጵያውያን በሙሉ ተባብረው በመከተል ብቻ ሳይሆን ከዚህ በፊት በማንኛውም ሌላ ጉዳይ በቁጣ ገንፍለው ተነስተው ከማያውቁበት፣ እጅግ በላቀ ሁኔታ ወድያው በቁጣ ገንፍለው ይነሳሉ። ሁሉም ኢትዮጵያውያን እርስዎን ተከትለው በመትመም ያንን ነፃነት ለዘላለም የግላቸው ሃብት ያደርጉታል። የኢትዮጵያ አምላክ ከርስዎ ጋር ይሂድ። ያበርታዎ። የህን ታሪካዊ ተልእኮም ለመፈጸም ጥንካሬና ፍዑም ጨዋነትን ያላብስዎ።**

**ከሙሉ የአክብሮት ሰላምታ ጋር፤**
**ገ. ኢ. ጐርፉ**
ፌብርዋሪ 20, 2005

ይህን ደብዳቤ ወደ አማርኛ በመተርጐም ለረዱኝ ወዳጄ፣ ለአቶ ቦጋለ ዳኘ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

## **Notes**:

1) http://news.bbc.co.uk/2/hi/africa/4232107.stm underlining added by the author.
2) http://www.aigaforum.com/Gorfu-nile.htm April, 2004
3) Gebre Tsadik Degefu: *The Nile: Historical, Legal and Developmental Perspectives*, Trafford Publishing, ISBN 1-4120-0056-4
4) Ibid. Werner Muzinger… articulated… (Egypt's) policy towards Ethiopia as follows: **"Ethiopia with a disciplined administration and army, and a friend to the European Powers, is a danger to Egypt. Egypt must either take over Ethiopia and Islamize it, or retain it in anarchy and misery."**
5) Fact File about the Nile River, http://www.mbarron.net/Nile/fctfl_nf.html
6) *Association of Oil Pipe Lines* http://www.aopl.org/
7) http://www.mbarron.net/Nile/fctfl_nf.html the map.
8) Nile Basin Initiative http://nile.ca/doc/kim1.htm
9) UN Millennium Development Plan under "'Ensure Environmental Sustainability' **Target 10**: Halve, by 2015, the proportion of people without sustainable access to safe drinking water and basic sanitation." http://unmp.forumone.com/eng_low_res/TF1-overviewEngi-1LowRes.pdf
10) http://www.bbc.co.uk/radio4/today/reports/international/watershortage_20050203.shtml